# ለተመላሽ ኢትዮጵያውያን የቀረጥ ነፃ መብት የሚሰጠው መመሪያ ተሻረ

በውጭ ሃገር ቆይተው ወደ ሃገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን የግል እና የቤት መገልገያ ዕቃዎችን ከታክስና ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚችሉበትን ሁኔታ የሚደነግገው መመሪያ 7/96 ተሻረ::

አቶ በለጠ አህመድ፣ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የህግ አገልግሎት የሥራ ሂደት ጊዜያዊ ዳይሬክተር ግንቦት 13/2001 በባለሥልጣኑ መ/ቤት የስብሰባ አዳራሽ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳሉት በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ ሃገር ቆይተው ወደ ሃገራቸው ለሚመለሱ ኢትዮጵያውያን ከ1996 ጀምሮ ተሰጥቶ የነበረው የግል እና የቤት መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ የማስገባት መብት ከሚያዝያ 08/2001 ጀምሮ መቋረጡን አስታውቀዋል::

በዳይሬክተሩ መግለጫ መሠረት በሥራ፣ በትምህርት፣ በህክምና በሌሎች ምክንያቶች በውጭ ሃገር ቆይተው ወደ ሃገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያዊያን፣ በውጭ ሃገር የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤቶች ሲያገለግሉ ቆይተው የሚመለሱትን ጨምሮ የግል እና የቤት መገልገያ ዕቃዎቻቸውን ቀረጥና ታክስ እየከፈሉ ማስገባት ይችላሉ::

መመሪያ 7/96 በተለያዩ ጊዜ በወጡ መመሪያዎች ሲሻሻል ቆይቶ ሚያዝያ 8/2001 በቁጥር 1.6/5/1 ባለሥልጣኑ ባስተላለፈው ሰርኩላር መሻሩን ዳይሬክተሩ አስገንዝበዋል::

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ መመሪያ 7/96 የተሻረው በቀረጥ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎች አጠቃቀም ህግን የተከተለ ባለመሆኑ ነው:: በቀረጥ ነፃ ወደ ሃገር የገባን ዕቃ ለንግድ ወይም ትርፍ ለሚያስገኝ ሥራ ጉዳይ እንዳይውል ወይም ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ይሁን በሌላ በማናቸውም መንገድ እንዳይተላለፍ የሚደነግገውን ህግ በመጣስ ተመላሽ ኢትዮጵያውን የቀረጥ ነፃ መብታቸውን ያለአግባብ ሲጠቀሙበት መስተዋሉን ጠቁመው ይህ ሁኔታ በመንግስት ገቢ አሰባሰብ እና በህጋዊ ንግድ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ተፅዕኖ ከምንጩ ለማድረቅ በተወሰደው ርምጃ መመሪያ 7/96 መሻሩን አስታውቀዋል::

ይሁን እንጂ በሌሎች ህጐች መመሪያዎችና ኢትዮጵያ በፈረመችባቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች መሠረት የተሰጡ የቀረጥ ነፃ መብቶች ዛሬም ያልተቋረጡ መሆናቸውን ዳይሬክተሩ ጠቁመው በዚህ መሠረት በሃገራችን የሚገኙ የውጭ ሃገር ዲፕሎማቶችና የቆንስላ ሚሲዮኖች፣ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችና የዕርዳታ ድርጅቶች፣ ኢንቨስተሮች፣

*በኢትዮጵያ ለመኖር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ ግለሰቦችና እውነተኛ ሃገር ጐብኚዎች* /Bona fide tourists/ *የመብቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ዳይሬክተሩ ገልፀዋል፡፡*

*የመብቱ ተጠቃሚዎች ዕቃዎቻቸውን የሚያስገቡበትን ሁኔታ ዳይሬክተሩ ሲገልፁ በሃገራችን የሚገኙ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚሲዮኖች የዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ለታወቁ አገልግሎቶች የሚያስገቡዋቸው ዕቃዎች በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ /ለ/ መሠረትና በሌሎች ህጐች መመሪያዎችና ኢትዮጵያ በፈረመችባቸው ስምምነቶች መሠረት የሚስተናገዱ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡*

*እንዲሁም ለኢንቨስትመንት ወደ ሃገር የሚመጡ ባለሃብቶች በሃገር ውስጥ ከብር 5 ሚሊዮን ባላነሰ ኢንቨስት ማድረግ የሚችሉ መሆናቸው እየተረጋገጠ በኢትዮጵያ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ጠቅላላ ዋጋቸው ከ10,000 የአሜሪካ ዶላር የማይበልጡ የግልና የቤት መገልገያ ዕቃዎችን /ተሽከርካሪን ሳይጨምር/ ማስገባት እንደሚችሉ ዳይሬክተሩ አስገንዝበዋል፡፡*

*በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ ግለሰቦችና እውነተኛ ሃገር ጐብኚዎች /ቱሪስቶች/ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ /ለ/ ቁጥር 2 በተመለከተው መሠረት እቃዎቻቸውን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ ሃገር ማስገባት የተፈቀደላቸው መሆኑን ዳይሬክተሩ ጠቁመው የዕቃዎቹ ጠቅላላ ዋጋ ከ5000 የአሜሪካን ዶላር መብለጥ እንደሌለበት አስታወቀዋል፡፡*

*በጉዞ ላይ በነበሩና ለጉምሩክ ስነ ስርአት አፈፃፀም በቀረቡ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያዎች ሰርኩላሩ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ወር ያህል በነባሩ መመሪያ መሠረት እንዲስተናገዱ የተፈቀደ መሆኑን ዳይሬክተሩ ገልፀዋል፡፡*

## ሁለተኛ መደብ /ለ/

## ከማናቸውም ቀረጥ ነፃ የሆኑ /ያልተመደቡ/

**መግለጫ**

በጉምሩክ የገቢ እቃዎች ዲክለራሲዮን ተሞልተው የሚቀርቡት እቃዎች በዚህ ታሪፍ አንደኛ መደብ መሠረት ለታሪፍ አመዳደብ እና ለስታትስቲካዊ ስራ ሲባል በተጨማሪ መመደብ ያስፈልጋቸዋል።

### የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው ድርጅቶች፣ ግለሰቦች፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች ወይም የነዚሁ ወኪሎች ለሚያስመጡአቸው እቃዎች የተሰጡ ጠቅላላ የቀረጥ ነፃ መብቶች።

### 1. የዲፕሎማቲክስ እና የከንሱሰር መልእክተኞች፡-

በሁለት ወገን ስምምነቶች መሠረት፣ የሚከተሉት የቀረጥ ነፃ መብቶች ለመልእክተኞች እና ለሹማምንት ይሰጣሉ።

ሀ/ ማናቸውም እቃዎች፣ የሞተር ተሽከርካሪዎች ጭምር፣ ለዲፕሎማቲክ ወይም ለኮንሱላር መልእክተኞች የታወቀ አገልግሎት መጠቀሚያነት የሚመጡ።

ለ/ የቤት እቃዎች፣ የቤት ምቾት መጠበቂያዎች እና ማስዋቢያዎች እና እቃዎች፣ የሞተር ተሽከርካሪዎች ጭምር፣ ለዲፕሎማቲክ ሹማምንት የግል መጠቀሚያነት በማናቸውም ጊዜ የሚመጡ።

ሐ/ የቤት እቃዎች፣ የቤት ምቾት መጠበቂያዎች እና ማስዋቢዎች እና እቃዎች፣ የሞተር ተሽከርካሪዎች ጭምር የኮንሱላር ሹማምንት ተሹመው ሲመጡ ለመጀመሪያ ጊዜ

ከደረሱበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለግል መጠቀሚያነት የሚያስመጡአቸው::

## 2. <u>ጓዝ የግል እቃዎች፣ የሚከተሉት:-</u>

### ሀ/ <u>በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ ግለሰቦች</u>

ጓዝ፣ መንግደኞች የሚይዟቸው እቃዎች እና ንብረት ወይም መንገደኞች ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት /3/ ወራት ውስጥ በማናቸውም የጉምሩክ ጣቢያ የሚደርሱ ወይም ጉምሩክ በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የሚመጡ እቃዎች:-

1/ አስፈላጊ እና ተገቢ ልብሶች፣ የግል ጌጣጌጦች እና የንጽሕና መጠበቂያ እቃዎች::

2/ ለቤት የሚያገለግሉ እቃዎች፣ የቤት እቃዎች፣ ምንጣፎች፣ ስእሎች ከብርጭቆ የተሰሩ እቃዎች፣ ጨርቃጨርቆች፣ ሸክላዎች፣ ቢላዋ፣ ሹካና ማንኪያዎች፣ ሳህኖች፣ የስፌት መኪናዎች የመሳሰሉት፣ እና በተጨማሪ ባይኖኩላሮች፣ ካሜራዎች /ባለ 8፣ 9.5 እና 16 ሚሊ ሜትር ሲኒማቶግራፊክ ካሜራዎች ጭምር/፣ የስፖርት እቃዎች፣ ቀላል የሆኑ የጽሕፈት መኪናዎች እና አሻንጉሊቶች እና የመሳሰሉት፣ ወደ አገር ከመምጣታቸው በፊት የመንገደኞች የግል መገልገያዎች ወይም የቤት እቃዎች እና ለሽያጭ ያልታቀዱ ስለመሆናቸው ለጉምሩክ በቂ ማረጋገጫ ሲቀርብ::

3/ ሁለት /2/ ሊትር መጠጥ አልኮል ቢኖረውም ባይኖረውም::

4/ በቁጥር ከመቶ /100/ ያልበለጡ ሲጋሮች፣ በቁጥር ከሃያ /20/ ፓኬት ያልበለጡ ሲጋራቶች ወይም በክብደት ከአምስት መቶ /500/ ግራም ያልበለጠ ትንባሆ::

5/ የመንገደኛው የሙያ መሳሪያዎች እና የተግባረዕድ መሳሪያዎች::

ለ/ ከውጭ አገር የሚመለሱ ዜጎችና በተራድኦ ስምምነት የሚመጡ የውጭ ዜጎችን የግል መገልገያ እቃዎች በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት /ማሻሻያ/ ደንብ ቁጥር 6/1988 መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፣

ሐ/ <u>እውነተኛ /በናፋይድ/ አገር ጎብኚዎች ጓዝ</u>፡- ቱሪስቶች የሚይዟቸው እቃዎች እና ንብረት፡-

1. አስፈላጊና ተገቢ ልብሶች፣ የግል ጌጣጌጦች እና የንጽሕና መጠበቂያ እቃዎች፡፡
2. ሁለት /2/ ሊትር መጠጥ አልኮል ቢኖረውም ባይኖረውም፡፡
3. በቁጥር ከመቶ 100 ያልበለጡ ሲጋሮች፣ በቁጥር ከሃያ /20/ ፓኬት ያልበለጠ ሲጋሬቶች ወይም በክብደት ከአምስት መቶ /500/ ግራም ያልበለጠ ትንባሆ፡፡

በእውነተኛ አገር ጎብኚዎች አማካይነት የሚመጡ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይሸጡ የሚደረገው መከላከል እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለአገር ጎብኚዎች አስፈላጊ የሆኑ ወይም ለጉብኝት ዓላማ ተፈላጊ ናቸው የሚባሉ ማናቸውም ቀላል እቃዎች ወይም ጓዝ ጉምሩክ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## 3. <u>ዋንጫዎች፣ ሜዳሊያዎች እና ሌሎች ሽልማቶች ለስጦታ ብቻ ወደ አገር ሲመጡ /ለሽያጭ ያልተሰጡ/</u>

ሀ. በፈተና ብልጫ፣ በኤግዚብሽኖች ወይም በትእይንቶች ወይም በውድድሮች ወይም በስፖርት ለተገኙ ችሎታ፣ ለታወቁ ከለሰቦች አባላት እና ለሕዝብ የተሰጡ ሽልማቶች፡፡

ለ. ለጉብዝና፣ ለመልካም ጠባይ፣ ለርህራሄ፣ ለሥነጥበብ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለፈጠራ፣ ለምርታማነት፣ ለትምህርት፣ ለሳይንስ ብቃት ወይም ለተቀደሰ ሥራ ወይም ለሚያስመሰግን ሕዝባዊ ግልጋሎት የሚሰጡ፣

ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 3/ሀ/ እና 3/ለ/ ለተጠቀሱት ስጦታዎች የነፃ መብት ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ይፈፀማል፡፡

4. የኢትዮጵያ መንግስት መስሪያ ቤቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶች የሚያስመጧቸው እቃዎች በተመለተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት /ማሻሻያ/ ደንብ ቁጥር 6/1988 መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፣

5. የእሳት ቃጠሎ ማጥፊያ መሳሪያዎች

የእሳት ቃጠሎ ማጥፊያ ኬሚካሎች፣ ከእሳት ቃጠሎ ማምለጫዎችና ሌሎች መሳሪያዎች

6. ለሽያጭ ያልመጡ የንግድ ዕቃ ናሙናዎች፣ የሕክምና ናሙናዎችን ሳይጨምር

የንግድ እቃ ናሙናዎች ቀረጥ የሚከፈልባቸው መሆን ወይም አለመሆናቸው በባሕሪያቸው እና ወደ አገር በሚመጡበት ሁኔታ ይወሰናል፡፡ ዋና ዋና ምድቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ የንግድ ዋጋ የሌላቸው ናሙናዎች የንግድ ዋጋ እንደሌላቸው ግልጽ ማረገጫ ከቀረበ ከቀረጥ ነፃ እንደሆኑ ይፈቀዳል /ለምሳሌ በመጽሐፍ መልክ ያሉ ቁርጥራጭ ጨርቆች፣ ሶሉ ላይ የተበሳ የአንድ እግር ጫማ፣ ወዘተ/

ለ/ የንግድ ዋጋ ከሌላቸው ሌላ ከአንድ ዩኒት ሳይበልጡ የሚመጡ፣ እና ለቆራረጡ የማይችሉ ናመናዎች፣ ከቀረጥ ነፃ ሲገቡ ይችላሉ፡፡ ይህም የሚሆነው፡-

1. ለኤግዚብሽን ወይም ለትርኢት የሚውሉ ሲሆን
2. በየዓነታቸው ከአንድ ዩኒት የማይበልጡ ሲሆን

ሐ/ ተመልሰው እንዲወጡ የታቀዱ ናመናዎች፣ በጉምሩክ አዋጅ እና የሕግ ክፍል ማስታወቂያ መሠረት በጊዜያዊነት ወደ አገር ሲገቡ ይችላሉ፡፡

ማስታወሻ ማናቸውም ዓይነት የገበያ ዋጋ ያላቸው ናሙናዎች፣ ለሽያጭ እንደሚውሉት ተመሳሳይ እቃዎች ተመሳሳ ቀረጥ እና ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

7. አገር ውስጥ ገብተው የማይቀሩ በተደጋጋሚ እቃ የሚመጣባቸው ኮንቴይነሮች፣ ሳጥኖች፣ ጣሳዎች፣ ጠርሙሶች፣ ማድጋዎች እና ሌሎች መያዣዎች፣ በውሳጣቸው ቀረጥ የማከፈልባቸው ማናቸውም እቃዎች ተሞልተውባቸው ሊመጡ ወይም በውስጣቸው ላሉት የንግድ እቃዎች መጠቅለያ ሆነው ሲመጡ፡፡

8. በአገር መከላከያና ለሕዝብ ደህንነት የሚውሉ የጦር ማሳሪያዎች

9. ለአካል ጉዳተኞች የሚያገለግሉ ልዩ እቃዎችና መሳሪያዎች

10. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ የልማት እቃዎችን በተመለከተ ስለተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት /ማሻሻያ/ ደንብ ቁጥር 6/1988 ይመልከቱ፣